# ምዕራፍ ሁለት

## ሀ. ሥርዓተ ቍርባን

1. <u>ቅዱስ ቁርባንን ለመቀበል የሚገቡ ቅድመ ዝግጅቶች</u>

በቅድሚያ አንድ ክርስቲያን ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን ከመቀበሉ አስቀድሞ አምስቱን አዕማደ ምስጥር ቢማር ቢያውቅ የተገባ ነው። ምክንያቱም የሚቀበለው ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም የማን ሥጋና የማን ደም መሆኑ ለማወቅ ይረዳዋል።

ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስም በምስጢራዊ ንግግሩ አምስት ቃላትን በአእምሮዬ ልናገር እወዳለሁ ብሏል (1ኛቆሮ14 ቁ.19):: እን ዲሁም "በእንተ ትምህርተ ኅቡዓት ቅድመ ዘትትነገር እምቅርስፎራ ለምእመናን ኅቡዓት" ሥጋዉን ደሙን ከመቀበል አስቀድሞ የሚነገር አምስቱ አዕማደ ምስጢር ይህ ነው፤ እንዳለ በትምኅርተ ኅቡዓት::

<u>አምስቱ አዕማደ ምስጥር የተባሉትም፦</u>

1ኛ. ምስጢረ ሥላሴ

2ኛ. ምስጢረ ሥጋዌ

3ኛ. ምስጢረ ጥምቀት

4ኛ. ምስጢረ ቁርባን

5ኛ. ምስጢረ ትንሣኤ ሙታን ናቸው።

1.1 <u>ምስጢረ ሥላሴ</u>፦ በዚህ ርእስ ልንማረው የሚገባ ስለሥላሴ አንድነትና ሦስትነት ሲሆን ምስጢር የተባለበትም ምክንያት ሥላሴ ሦስት ሲሆኑ አንድ፣ አንድ ሲሆኑ ሦስት ናቸው ብሎ አምኖ ይህ ሊሆን እንደምን ይቻላል ብሎ የፍጡር ልቡና አስቦ እና አንደበቱም ተናግሮ ሊፈጽመው ስለማይችል ምስጢር ተብሏል። (ዘፍ 1 ቁ 26፤ 3ቁ 22፤ 16 ቁ7) (ዘዳ3 ቁ 6-16) (መዝ32 ቁ 6) (ኢሳ6 ቁ 3) (ማቴ 28 ቁ 19)

1.2 <u>ምስጢረ ሥጋዌ</u>፦ በዚህ ርዕስ ስለአምላክ ሰው መሆን የምን ማርበት ነው። ምስጢር የተባለበት ምክንያት፦

❖ ምሉዕ አምላክ የሰውን ነፍስና ሥጋን ተዋሕዶ ውሱን ሥጋ ሲሆን፣ ውሱኑ ሥጋ ደግሞ የመለኮትን ባሕርይ ገንዘብ አድርጎ ምሉዕ አምላክ ሆነ። አምላክ ሰው ሆነ ሰው አምላክ ሆነ:: አማኑኤል ተባለ "ድንግል ትጸንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች" ኢሳ.7÷14 አማኑኤል ማለት ትርጓሜውም እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የሚል ነው::

ማቴ.1 ቁ.23 ይህም ማለት እግዚአብሔር ከሥጋችን ሥጋ ከነፍሳችን ነፍስ ነስቶ ከእኛ ጋር አንድ አካል አንድ ባሕርይ ሆነ ማለት ነው፡፡ ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስም የዮሐንስ ወንጌል 1 ቁ. 1 ላይ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ ካለ በኋላ ዝቅ ብሎ ቁ. 14 ላይ ያ በቅድምና የነበረው ቃልም ሥጋ ሆነ ብሏል፡፡

- ረቂቁ ግዙፍ፣ ሆነ ስንል የማይታየውና የማይዳሰሰው አም ላክ ግዙፍ የሚዳሰስ ሰው፣ የሚዳሰሰው ግዙፉ ሥጋ ደግሞ የማይዳሰስ የማይታይ ረቂቅ አምላክ ሆነ ማለታችን ነው።
- ልዑል አምላክ ልዕልናውን ሳይለቅ ትሑት ሥጋን ሲለብስ ትሁት ሥጋ ደግሞ ትሕትናውን ሳይለቅ ልዑል አምላክ ሆኗል።
- ነገር ግን አምላክ እንዴት ሰው፣ ሰው እንዴት አምላክ፣ ምሉዕ እንዴት ውሱን፣ ውሱኑ እንዴት ምሉዕ፣ ልዑል እንዴት ትሑት፣ ትሁቱ እንዴት ልዑል፣ ረቂቁ እንዴት ግዙፍ፣ ግዙፉ እንዴት ረቂቅ፣ ኃያሉ አምላክ ደካማ ሥጋን፣ ደካማ ሥጋ ኃያል መለኮት መሆኑ፣ ቅድምና የሌለው ሥጋ ቀዳማዊ አምላክ መባሉ፣ ዘመን ለማይቆጠርለት አምላክ ዘመን መቆጠሩ፣ እንዲህ ያለው ነገር እንዴት ሊሆን ይች ላል ብሎ ልብ ሊመረምር ቃልም ሊናገረው እና ሊፈጽ መው ስለማ ይችለው ምስጢር ተብሏል። እምኔኪ ለብሰ አማኑኤል ልብሰተ ሥጋ ዘኢይተረጎም ንባቡን አቅንቶ በጥቅሉ ሲተረጎም የማይመረመር አማኑኤል ካንቺ በማይመ ረመር ተዋሕዶ ሥጋን ለበሰ ብሏልና ቅዱስ አባ ሕርያቆስ (ኢሳ7 ቁ 14) (ሚኪያ5 ቁ 2) (ዮሐ1 ቁ 14) (ቅ.ማር)



1.3 <u>ምስጢረ ጥምቀት</u>፦ በዚህ ርእስ ሰው ሁሉ ከአብራከ መንፈስ ቅዱስ ከማኅጸነ ዮርዳኖስ ተወልዶ የሥላሴን ልጅነት የሚማር በት ነው። ምስጢር የተባለበትም ምክንያት፡

ካህኑ (ቄሱ) ውኃዉን በብርት (በሰን) አድርጎ አሐዱ አብ ቅዱስ አሐዱ ወልድ ቅዱስ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ ብሎ በባረከው ጊዜ ውሃው ተለውጦ ከጌታ ቀኝ ጐኑ በዕለተ ዓርብ የፈሰሰውን ማየገቦ (የጎን ውሃ) ይሆናል። ይህ እንደምን ሊሆን ይችላል ብሎ ልብ ሊመረመረው ቃል ሊናገረው ስለማይ ችል ምስጢር ተብሏል። ሰው ሁሉ የሥላሴን ልጅነት የሚያገኘው ከጌታ ከቀኝ ጎኑ በፈሰ ሰው ማየገቦ (ውሃ) ተጠምቆ ነውና፡፡ (መዝ 67ቁ 22፤28ቁ 3፤ 76ቁ 16፤ 113ቁ 5-7) (1ኛ ቆሮ10 ቁ 2) (የሐ.ሥ1 ቁ 5) (ማቴ 3 ቁ 16-17 ፤28 ቁ 19) (ዮሐ.3 ቁ 3-14)

1.4 **ምስጢረ ቁርባን፦** በዚህ ርእስ ስለ ክርስቶስ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም የምንማርበት ክፍል ነው። ምስጢር የተባለበትም ምክንያት ካህኑ በጸሎተ ቁርባን ጊዜ ኅብስቱን በጸሕል ወይኑን በፅዋ አድርጎ በተሰጠው ሥልጣን "ይረስዮ" (ኀበኑ) ብሎ በባረከው ጊዜ ኅብስቱ ተለውጦ ሥጋ መለኮት ወይኑም ተለውጦ ደመ መለኮት ይሆናል። ይህ ሲሆን እንዴት ይችላል ብሎ ልብ ሊመረምረው ቃል ሊናገረው ስለማይችል ምስጢር ተብሏል። (ማቴ 26 ቁ 26-28) (ዮሐ6 ቁ 56-59) (1ኛቆሮ11ቁ 23-26)

1.5 **ምስጢረ ትንሣኤ ሙታን፦** በዚህ የትምህርት ክፍል ስለ ሙታን ትንሣኤ የምንማርበት ሲሆን ምስጢር የተባለበትም ምክንያት ሰው ከሞተ ከፈረሰ ከበሰበሰ በኋላ እንደገና አካል ገዝቶ በዕለተ ትንሣኤ ይነሣል ብሎ ማመን ነው። ይህ ሲሆን እንዴት ይችላል ብሎ ልብ ሊመረመረው ቃል ሊናገረው ስለማይችል ምስጢር ተብሏል። (ማቴ 22 ቁ 22-33) (1ኛ ቆሮ15 ቁ 12-57) (ተሰሎ4 ቁ 14-18)

## 2. ንስሐ መግባት

ንስሐ ለመግባት ቀጠሮ አያስፈልግም፤ ሰዎች ነንና በምንኖርበት ዓለም እግዚአብሔርን ማሳዘናችን ስለማይቀር ሁልጊዜ ንስሐ መግባት አለብን:: "ስብአ ይወድቅ ጻድቅ ወስብዐ ይትነሣእ" ጻድቅ ሰው ሰባት ጊዜ ይወድቃል ሰባት ጊዜ ይነሣል ተብሏልና::

ማንኛውም ክርስቲያን ኃጢአቱን በደሉን በንስሐ ውሃ ተለቃልቆ ወደ ሥጋ ወደሙ መቅረብ ይገባዋል:: ኃጢአትን መዘንጋትና መሰወር አይገባም:: "ኃጢአቱን የሚሰውር አይለማም" ይለናልና የእግዚአብሔር ቃል (ምሳ 28 ቁ 13) ስለዚህ ሰው ሁሉ ስለ ሚያውቀው በደል ትዝ ትዝ እያለው ንስሐ ገብቶ በማያውቀውና በዘነጋው ደግሞ ይቅር በለኝ ብሎ ወደ ቅዱስ ቁርባን ሊቀርብ ይገባል። እንዲሁም በጸሎተ ቅዳሴው ምስጋናችን "በከመ ምሕረትከ አምላክነ ወአከ በከመ አበሳነ" እያልን የምንጸልየው አቤቱ ይህን ቅዱስ ሥጋህን ክቡር ደምህን የምንቀበለው እንደ ይቅርታህ እንደ ቸርነትህ ነው እንጂ እንደኃጢአታችን ብዛት ቢሆን ባልተገባን ነበር በማለት የአምላክን መሐሪነት፣ ቸርነቱንና የእኛን አላዋቂነት በዳይነት እየተናገርን ንስሐ እየገባን መቅረብ ይገባናል። ንስሐ ሳንገባ ቅዱስ ቁርባን ብንቀበል ግን የጌታ ሥጋና ደም ዕዳ እንዳለብን ሐዋርያው ያስገነዝበናል። (1ኛቆር 12 ቁ 27)

2.1 የነፍስ ንጽሕና

የነፍስ ንጽሕና የተባለው እውነተኛ ግብዝነት የሌለው ፍቅረ እግዚአብሔር ፍቅረ ቢጽ ነው። በተለይ ቅዱስ ቍርባን ለመቀበል ስንዘጋጅ ልቡናን ከቂም በቀል አርቆ፣ የበደለ ክሶ፣ የቀማ መልሶ፣ የተጣላ ታርቆ፣ በፍቅር በትሕትና ሆኖ መቅረብ ነው። ያለፍቅር የሚሆን ነገር የለምና ሐዋርያው ስንኳንስ የጌታ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን ያህል ነገር ይቅርና ያለ ፍቅር ጸሎትና ምስጋናውም ከንቱ እንደሆነ ያስገነዝበናል:: "የሰው ሁሉ ቋንቋን ባውቅ የመላእክትን ቋንቋ ብናገር ባውቅ ፍቅር ግን ከሌለኝ ሲመቱት እንደ ሚጮህ ናስ እንደሚንሿሿ ጸናጽል ሆኜአለሁ ማለቱ ፍቅር ግን ከሌለኝ ሲመቱት እንደ ሚጮህ ጸናጽል ወይም ደወል መሆኔ አይደለም ወይም ግራቀኝ ሲመቱት እንደሚጮህ ከበሮ መሆኔ ሲል ነው" ብሎ በ1ኛ ቆሮ.13 ቁ.1 ጽፎልናል። እንዲሁም ፍቅር የሌለው ጸሎት ትሕትና የሌለበት ድንግልና እንኳ ጥቅም የለውም "ምንት ለድንግልና ዘአልቦ ትሕትና ምንትኑ በቍዔቱ ለጸሎት ዘአልቦ አፍቅሮት" ፍቅር የሌለው ጸሎት ትሕትና የሌለው ድንግልና ጥቅሙ ምንድነው ይለናል (በመጽሐፈ ዜና ሥላሴ) ስለዚህ በመቻቻል እንፋቀር ዘንድ እምነት ጨምርልን እንበለው:: እኔ እንደወደድኋችሁ እርስ በእርሳችሁ ተዋደዱ ስላለን ፍቅሩን እንደሻማ ያልብሰን አሜን!

2.2 የሥጋ ንጽሕና

የሰው ተፈጥሮአዊ አካሉ ሥጋዊ አካልና መንፈሳዊ አካል በመባል ይታወቃል:: ሥጋዊ አካሉ በገሀዱ ዓለም የሚታየው የሚዳሰሰው ሲሆን መንፈሳዊ አካሉ ደግሞ በዚህ በሥጋዊ አካሉ ውስጥ ሕልው ሆኖ የሚኖር የማይታይ ረቂቅ አካል ነው:: ሐዋርያውም በዚህም በሚሞተው ሥጋችሁ የማትሞት ነፍስ እንዳለች አስተውሉ ብሎናል::

ስለሆነም ይህ በገሀዱ ዓለም የሚዳሰሰው ሥጋችን የሰውነታችን ሁለተኛው ክፍል ስለሆነ ቅዱስ ቍርባን ለመቀበል ስናስብ ሰውነታችንን ልናጸዳው ንጹሕ ልብስ ቢቻል ነጭ ልብስ ልንለብስ ይገባናል:: አፍአዊ (ውጫዊ) የሥጋችን ንጽሕና ለውስጣዊው ንጽሐ ልቡና መታወቂያው ነውና "መስዋዕተ ወቍርባነ ኢፈቀድከ አላ ሥጋከ አንጽሕ ሊተ" መሥዋዕትንና ቍርባንን አልወደድከም፤ ሥጋህን አዘጋጅልኝ ንጹህ አድርግልኝ አለ እንዲ:: (መዝ.39 ቁ.6)

በዚህ ዕለት የሰማያዊ ሙሽራ የንጉሥ ክርስቶስ ታዳሚ ሆነን የሰርግ ልብስ ለብሰን በውስጥም በውጭም አምረን ሰምረን መቅረብ አለብን:: (ማቴ 22 ቁ.14)

3. **ልዩ ጥንቃቄ**

3.1 **በምንጣፍ አንድ ከመሆን መከለከል**

የሚቀድሱና የሚቈርቡ ሰዎች በጋብቻ ጸንተው የሚኖሩ ከሆነ ከመቀደሳቸው እና ከመቈረባቸው በፊት 3ት ቀን በምንጣፍ አንድ ከመሆን ይጠበቁ። ከቈረቡ በኋላ 2ት ቀን ስለ ሥጋ ወደሙ ክብር ሲባል መጠበቅ ይገባል።

3.2 **ርስሐት ዝንየት (ሕልመ ሌሊት)**

ሰው ዝንየት ካጋጠመው በዚያ ቀን መቈረብ አይገባም። ነገር ግን ሰውነትን አጽድቶ በቀ ጣዩ ዕለት መቈረብ ይቻላል።

3.3 **መጾም**

በሚገባ ሳይጾም ማንም ሰው ሥጋውን ደሙን አይቀበል:: (ፍት. መን. አን.13 ቁ 512) ሥጋውን ደሙን ለመቀበል ባሰቡ ዕለት ለ18 ሰዓታት ያህል ከእህል ከውሃ መጠበቅ (መከ ልከል) ይገባል። ምክንያቱም ጌታም ከሌሊቱ 9 ሰዓት እስከ ቀኑ 9 ሰዓት በድምሩ ለ18 ሰዓት ያህል ልዩ ጸዋትወ መከራን ከተቀ በለ በኋላ መራራ ሐሞትን ቀምሷል፣ እኛም ከተመገብነበት ከ18 ሰዓት በኋላ የበላነው የጠጣነው ከሰውነታችን ስለሚዋሐድ፣ ለአፋችን ምሬት ይሰማናል። በዚህም የጌታ ሕማሙን፣ ሞቱንና የቀመሰውን መራራ ሐሞት እናስባለን።

ለምሳሌ ያህል፦ ቅዳሜ ለመቍረብ ካሰብን የጌታ ክቡር ደሙ ከፈሰሰበት ከዓርብ 9 ሰዓት ጀምሮ ጾመን በነጋታው ቅዳሜ ድርገት በሦስት ሰዓት ገደማ ስለሚወርድና ስለ ምንቈርብ እስከዚህ ያለው ሰዓት ብናሰ ላው 18 ሰዓት ይሆናል።

ነገር ግን ሕፃናት በሰንበት እንዲቈርቡ ከተፈለገ የግድ 18 ሰዓታት ያህል ይጹሙ ተብሎ አይገደዱም፤ በአእምሮ ጠባይ ሕጻ ናት የነበሩ የአበው ሐዋርያት ምሳሌዎች ናቸውና። ነገር ግን በጊዜ ተመግበው እንዲተኙና ማለዳ ለቅዳሴው እንዲነቁ ማድረግ ነው::

4. **ለመቍረብ የሚያበቁና የማያበቁ ምክንያቶች**

ሀ. ከምዕመናን በስተቀር ያላመኑ ሰዎች ሥጋውን ደሙን ሊቀበሉ አይገባቸውም:: (ፍት.መን. 13 ቁ 54)

ለ. ቅዳሴ ሲጀመር ያልነበረ፣ ያላስቀደሰ ካህኑም ማቁረብ መቍረብ፤ ምእመኑም መቍረብ አይገባም። (ፍት.መን. 13 ቁ 495)

ሐ. በንስሐ የተለየ ሰው ለሞት የሚያበቃ ደዌ በታመመ ጊዜ ሥጋውን ደሙን ከማቀበል አይከልክሉት ቢድንም አንተ ንስሐ ይገባሃል ንስሐህን ተቀበል ብለው ሥጋውን ደሙን ከመቀበል አይከልክሉት:: (ፍት.መን. 13 ቁ 505)

መ. በሚገባ ሳይጾሙ ሥጋወደሙን መቀበል አይገባንም:: (ፍት. መን. 13 ቁ 512)

ሠ. ቂም በቀል ያለበት የዝሙትና የስካር መንፈስ ያለበት ሰው ይህን ሁሉ በንስሐ ሳያርቅ መቀበል አይገባውም:: (ፍት.መን. 12 ቁ 415) (1ኛ ቆሮ11 ቁ 27)

5. <u>ለሥጋ ወደሙ አጋፋሪ አያስፈልገውም</u>

ከዚህ በላይ ከብዙ በጥቂቱ ከምሉዕ በከፊሉ የተጠቀሱትን ለቊርባን የሚያበቁ መጠይቆችን ሰው ሁሉ እንደተቻለው ይጠቀም በት ዘንድ አስቀድሞ ራሱን ይመረምር ዘንድ ከአስተዋለ ለሥጋ ወደሙ አጋፋሪ አያስፈልገውም:: ይህንን ስንል የሚያስተና ብር ሳዕከ ቤተክርስቲያን አይኑር ማለታችን አይደለም እየአንዳንዱ በራሱ ዳኝነት በልቡናው ፈራጅነት ልቀበል ይገባኛል ወይስ አይገባኝ ይሆን ብሎ አመዛዝኖ ይቀበለው ዘንድ ይገባል ማለት ነው። ይህም ቢሆን ሰው ምን ቢጾም፣ ምን ቢጸልይ፣ ምን ቢሰግድ፣ ምን ቢመጸውት፣ ማሰሪያው ቅዱስ ቊርባን መሆን እንዳለበት ይታመናል::

ይልቁንም የእግዚአብሔርን መሐሪነት ይቅር ባይነቱን ተመ ራምሮ ልክና መጠን ወሰንና ድንበር የሌለውን ፍጹም ቸርነቱን፣ ፍጹም በማመን ይቀበል:: ምክንያቱም ያልወደቀ፣ ጌታ በምሕረቱ እሱ ያላነሣው ያልተሰበረ፣ እሱ በቸርነቱ ያልጠገነው የለምና፣ ከፍ ጥረት ወገን ከአንዲት ቅድስት ድንግል በስተቀር:: "እመሰ ኃጢአ ነ ትትአቀብ እግዚአ እግዚአ መኑ ይቀውም ቅድሜከ" አቤቱ የሰውን ሁሉ በደልን ብትተሳሰብ በፊትህ ለአንዲት ሰዓት መቆም፣ መቆየት የሚችል ማነው? ያለው ነቢዩ (መዝ.129 ቁ 3) ይህ የምናየው ብሩህ ሰማይም እንኳ በእርሱ ፊት ንጹህ አለመሆኑን እርሱ በቸርነቱ እና በይቅር ባይነቱ ሁሉን እየተወው መሆኑን ያስገነዝበናል:: (መላእክትም ስንኳ ማለት ነው)

6. <u>ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን</u>
<u>ከመቀበል በፊት የሚጸለይ ጸሎት</u>

ይህን ጸሎት ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን ለመቀበል ጌታ በቸርነቱ የመረጣቸው ሁሉ እንዲህ እያሉ ይጸልዩት ዘንድ ይገባል።

አቤቱ ጌታዬ እየሱስ ክርስቶስ ሆይ !!
ርኩስ ከሆንች ከቤቴ ጣራር በታች ትገባ ዘንድ የሚገባህ አይደለህም። (ማቴ.8 ቁ8) እኔ በዚህ ዓለም አሳዝኜሃለሁና በፈትህም ክፉ ሥራ ሠርቻለሁና፣ በአርአያህና በአምሳልህ

የፈጠርከው ነፍሴንና ሥጋዬን ትእዛዝህን በማፍረስ አሳድፌአለሁና፣ ሥራ ምንም ምን የለኝምና፣ ነገር ግን ስለ መፍጠርህና እኔን ለማዳን ሰው ስለመሆንህ፣ ስለክቡር መስቀልህም ማሕያዊ ስለሚሆን ስለሞትህም፣ በሦስተኛው ቀን ስለመነሣትህ፣ ጌታዬ ፈጣሪዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ከበደልና ከመርገም ሁሉ ከኃጢአትና ከርኩሰትም ሁሉ ታነፃኝ ዘንድ እለምንሃለሁ፤ እማልድሃለሁም። የቅድስናህንም ምሥጢር በተቀበልሁት ጊዜ ለወቀሳና ለመፈራረጃ አይሁንብኝ፤ ማረኝ፤ ይቅርም በለኝ እንጂ።

የዓለም ሕይወት ሆይ በርሱ የኀጢአቴን ሥርየት የነፍሴንም ሕይወት ስጠኝ እንጂ። በሁለት ወገን ድንግል በምትሆን በወለደችህ በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም በመ ጥምቁ በዮሐንስ አማላጅነት ክቡራን በሚሆኑ በመላእክት፣ በሰማዕታት ለበጎ ነገር በሚጋደሉ በጻድቃን ሁሉ ጸሎት እስከዘላለሙ ድረስ አሜን።

### 6.1 ሲቀበሉ የሚጸለይ ጸሎት

ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ይህ ምሥጢርህ በእኔ በደል አይሁንብኝ ሥጋዬንና ነፍሴን ለማንጻት ይሁንልኝ እንጂ እያሉ፣ ወይም ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ሥሉስ የሚለውን ምሥጋና በቃል ይዞ ማመስገን ነው።

### 6.2 ከተቀበሉ በኋላ የሚጸለይ ጸሎት

ጌታዬ አምላኬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ቅዱስ ሥጋህንና ክቡር ደምህን እነሆ ተቀበልሁ ለኃጢአቴ ማስተሥርያ ይሁነኝ ስለ በደሌም ሁሉ።

ሰውን የምትወድ ወልድ ዋሕድ ሆይ ምስጋናህን በአንደበቴ ሙላ። ምስጋናህን አመሰግን ዘንድ ቀድሞ አንተ ሰው የሆንክ በሉም የተገለጽህ እስከዘላለሙ ታድነኝ ዘንድ ነውና፣ ስለ ቅዱስ ስምህም ለዘላለሙ አዳንከኝ። ጌታዬ አምላኬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ በአገልጋይህ በዚህ በካህኑ እጅ ሥጋ ህንና ደምህን አንድ አድርገህ ለሰጠኸኝ ለአንተ ምስጋና ይገባሃል፤ አመሰግንሃለሁ፤ እለምንህማለሁ።

ከምእመናን ጋር አንድ እሆን ዘንድ ከወዳጆችህም ጋር ትቆጥረኝ ዘንድ ተቀበለኝ አሁንም ኀጢአቴን አትቁጠርብኝ ለኔ ስለ ሰጠኸኝ ፀጋህና በኔ ስላለችው ረድኤትህ አመሰግንሃለሁ።

### 7. ሥጋወደሙ

- ጥበብን ይገልጻል።
- ልቡናን ብሩህ ያደርጋል።
- ልበ ሰፊ ነገር አላፊ ትዕግሥተኛ ያደርጋል።
- በልሳን ሥጋ ቋንቋ ያናግራል።

- በልሳነ ነፍስ ምስጢር ያስተረጕማል።
- በክብር ላይ ክብርን ያጎናጽፋል።
- መድኀኒተ ሥጋ መድኃኒተ ነፍስ ሕይወተ ሥጋ ሕይወተ ነፍስ ይሆናል።
- ደዌ ሥጋና ደዌ ነፍስን ያርቃል ጤናማ ያደርጋል።
- ሰላማዊ ጸጥተኛ ሰው በኑሮ ደስተኛና ፍቅር የመላው ሰው ያደርጋል።
- አምነውም ለሚቀበሉ ሰዎች ሁሉ ሕይወትን የሚያድል እሳት ማሕየዊ ነው (ቅ.ማር.)።

## 7.1 በቅዱስ ቊርባንነቱ አምነው በንስሐ ጸድተው ሥጋውን ደሙን ቢቀበሉ የሚገኝ ክብር

የክርስቶስን ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን በማመን የተቀበለ ሁሉ፦ ጌታ ዘበልዐሥጋየ ወሰተየ ደምየ ቦ ሕይወት ዘለዓለም (ሥጋዬን የበላ ደሜን የጠጣ ለዘላለም በሕይወት ይኖራል) ዮሐ. 6፥53 እንዳለው።

- ለዘለዓለም በሕይወት ይኖራል።
- **ልቡናውን ከቂም ከበቀል አርቆ ለሚቀበለው የዘለዓለም ምሕረትን ያጐናጽፋል።**
- **ከዝሙት ከርኵሰት ከስካር ርቀው ቢቀበሉ ልቡናን ከኀጢአት ያነጻል ዳግመኛ እንዳይበድል በንጽሕ ና በቅድስና እንዲና የሥጋንና የነፍስ ንጽሕና ያጐናጽፋል።**
- **ከጥርጥር ተለይተው ቢቀበሉት በሃይማኖት እንዲጸኑ ይረዳል።**
- **የበደሉትን ክሰው የቀሙትን መልሰው የተቀበሉት እንደሆነ በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስን እንደሸማ ያለብሳል።**

## 7.2 ሥጋወደሙ በንስሐ ሳይመለሱና ሳያምኑ ቢቀርቡ የሚያስከትለው ጉዳት

- የማይላመጥ የአድማስ ደንጊያ ነው። በዚህም የሚያስከትለውን የመከራ ጽናት ለመናገር ነው። የደንጊያ ንፍሮ ወይም የብረት ቆሎን ማላመጥ እንደማይቻልም በአግባቡ ሆነው ከአልተቀበሉት የሚያስከት ለውንም መከራ ጽኑዕ ነው።
- በኀጢአት ላይ ኀጢአትን የሚጨምር ነው። (ኀጢአትን ማስተሥረይ ቀርቶ በደለኛ ያደ ርጋል)
- ደዌ ሥጋ ደዌ ነፍስን የሚያመጣ ነው።
- እንደ ባቢሎን እሳት የሚያቃጥል የሚልጥ የሚግጥ እሳት ይሆናል።

- ልቡናን በኀጢአት ያደነድናል እንደ ይሁዳ ለሌላ በደል ያዘጋጃል::
- በመከራ ላይ መከራን ያመጣል:: "እንዘ ኢይደልዎ ዘበልዖ ለዝንቱ ኅብስት ወለ ዝንቱ ጽዋዐ በልዐ ለርእሱ ደይኖ ወመቅሰፍቶ" ሳይገባው ከዚህ ሥጋና ደም የበላ ለራሱ መቅሰፍትን ሰበሰበ እንዳለው ሐዋርያው:: (ቆሮ. 11 ቁ. 27)

**እግዚአብሔር አምላክ ሳይገባን ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን ተቀብለን በበረከት ፈንታ መርገምን፣ በሕይወት፣ በድኅነት ፈንታ መከራና ሞትን፣ መቅሰፍትን ገንዘብ ከማድረግ ያድነን ይሰውረን:: አሜን!!**

90

## 8. <u>የአቀራረብ ቅደም ተከተል</u>

ገባሬ ሠናዩ ቄስ በመጀመሪያ ሥጋውን በእጅ አንሥቶ ለራሱ ተቀብሎ ለሌሎች ያቀብላል። ንፍቁ ቄስ ደግሞ ደሙን በጽዋ ይዞ መጀመሪያ ለገባሬ ሠናዩ ካህን ያቀብለውና ለራሱ ይቀበላል። በመቀጠል ለዲያቆናቱ በእርፈ መስቀል አቀብሏቸው ለገባሬ ሠናዩ ዲያቆን ጽዋውን ይሰጠዋል። ከዚህ ቀጥሎ ለቁራቢዎቹ ገባሬ ሠናዩ ቄስ ሥጋውን በእጁ ሲያቀርብ ገባሬ ሠናዩ ዲያቆን ደግሞ ደሙን በዕርፈ መስቀል ያቈርባል ንፍቁ ቄስ ዲያቆኑም ሥጋውንም ደሙንም በእጃቸው አይነኩም።

### 8.1 <u>የአቈራረቡ ተራ</u>

1. ሊቃነ ጳጳሳት
2. ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት
3. ቆሞሳት
4. ቀሳውስት እነዚህ ሥጋውን ከታቦቱ ላይ ሳይነሣ በመንበር ላይ እንዳለ በቅድሚያ በየማዕረጋቸው ይቀብላሉ
5. ዲያቆናት በመቅደስ ይቈርባሉ
6. ከንፍቀ ዲያቆናት ጀምሮ ሁሉም በየማዕረጉ በቅድስት ይቀበላሉ
7. ከዐጸውተ ኆኅዋውና ከዲያቆናውያት በኋላ በዕለቱ ክርስትና የተነሡ ይቀበላሉ። ከእነርሱም ለ40ና ለ80 ቀን ሕፃናት ቅድሚያ ይሰጣል
8. ከሕፃናት ቀጥሎ ደናግል
9. የቀሳውስት ሚስቶች
10. የዲያቆናት ሚስቶች
11. መነኮሳት ምዕመናን

12. መነኮሳይያት
13. ምእመናን ወንዶችና ሴቶች ተራቸውን ጠብቀው በ'
ማዕረጋቸው ይቀበላሉ።

9. **ቅዱስ ቁርባን ከተቀበሉ በኋላስ!**

❖ ቅዱስ ቍርባን ከተቀበሉ በኋላ ወዲያው ቅዳሴ ጠበሪ መጠጣት አይገባም ቆመው ያስቀደሱበት ቦታ በመሄ ድርገት እስኪመለስ ድረስ መቆም ይገባል።

❖ በአፍ ውስጥ ትንኝና የመሳሰሉት ተሐዋስያን እንዳ ገቡ አፍን በመሃረብ መሸፈን።

❖ ከሠርሆተ ሕዝብ አስቀድሞ (ከስንብት አስቀድሞ ማለት እትዉ በሰላም በሰላም ግቡ ከመባሉ አስቀድሞ) ሥ ውን ደሙን የተቀበሉ ሁሉ በሌላ ዛቲ (ጸሪቀመበለት አፋቸውን አያድፉ ቅዳሴ ጠበሉም ከአፋቸው አይንጠ (ፍት.መን አን. 13 ቁ 527)

❖ ከቤተ መቅደስ ሳይጋፉ በቀስታ ወጥቶ በደጀ ሰላ ዛቲ (ጸሪቀመበለት) ቀምሶ አፍን ማደፍ ይገባል።

9.1 **ከቁረቡ በኋላ ጥንቃቄው**

❖ የተቀበልነው ነፍስ የተለየው መለኮት የተዋሃደ ሥጋ አምላክ ነው። አባቶቻችሁ በምድረ በዳ ኅብስተ መና በልተው እንደሞቱ ተብሎ በቅዱስ ወንጌል የተ ገረለት (ዮሐ.6 ቁ 58) እንደሚለው ምድራዊ ኅብስት ያይደለ ከሰማየ ሰማያት የወረደ ሰማያዊ ኅብስት እንደ መሆኑ መጠን ፈጽመን ብናከብረው እንከብራለን ስለ ዚህ በቆረቡ ዕለት:-

❖ ብዙ ማውራት አይገባም።

❖ ጸብና ክርክር ካለበት ቦታ መሄድ አይገባም።

❖ ወደፍርድ ቤት መሄድ መሟገት አይገባም።

❖ አብዝቶ መመገብ አብዝቶ መጠጣት አይገባም።

❖ ዘፈን ጫጫታ ወደአለበት ወደ መዝናኛ ስፍራ ሄዶ መጫወት መዝፈን አይገባም።

❖ ከልብስ መራቆት አይገባም ቢቻል ሲቈርቡ የለበሱት ልብስ እንደለበሱ መዋል የተመረጠ ነው።

- ጥፍርን መቁረጥ አይገባም::
- ምራቅን እንትፍ ማለት አይገባም::
- ፀጉርን መላጨት አይገባም::
- በውኃ ልብስን ማጠብ ሰውነትንም መታጠብ አይገባም::
- ብዙ መንገድ መሄድ ብዙ ሥራ ለመሥራት ራስን ማዘጋጀት አይገባም። በዚህ ዕለት ፊጽሞ አርፎ ቅዱሳት መጻሕፍትን መንፈሳዊ መዝሙሮችን ማዳመጥ ይገባል።
- ወደ ሲኒማ ቤት መሄድ አይገባም።
- (ሥርዓተ ቅዳሴ ቁ 166) (ፍ.መን.)::

## ምዕራፍ ሦስት

## ሀ. ስንቀ ነፍስ

አንድ ሰው ታሞ ነፍሱ ከሥጋው እለይ እለይ እያለች ባለበት ሰዓት የሚቈርበው ቁርባን ስንቀ ነፍስ ይባላል:: በርግጥ ሰው ሁሉ በቅዱስ ቃሉ "ድልዋኒክሙ ንበሩ" ተዘጋጅታችሁ ኑሩ (ማቴ 29 ቁ.44) ተብሎ እንደተነገረን አንድ ክርስቲያን በሚኖርበት ዓለም መጻተኛነቱን ተገንዝቦ ንስሐ ገብቶ ብሥጋ ወደሙ ከብሮ መኖር ይገባዋል::

ነገር ግን በአጋጣሚ ሁኔታና እንዲሁም ንስሐ ለመግባት እድሉን ሳላገኘ ነገ ዛሬ ሲሉ ድንገት እንግዳ ጻእረ ሞት ከተፍ ቢል በአንዲት ጥምቀት አምኖ በኦርቶዳክሳዊት ተዋሕዶ ጸንቶ የኖረ ከሆነ ሥጋውን ደሙን ሊያቀብሉት ይገባል:: ክብር ምስጋና ይግባውና ወንበዴና ቀማኛ የነበረውን የዓለም በደለኛ የነበረውን ፈያታዊ ዘየ ማንን እንኳ ሊሞት ሲያጣጥር ባሰማው ድምጽ ስንቀ ነፍስ የሚሆን ማሕተመ ደሙን ሰጥቶት ከሁሉ አስቀድሞ ገነትን አውርሶታል ::

ስለዚህ ታሞ ሊሞት የሚያጣጥር ክርስቲያን ስንቀ ነፍስ ሊያቀብሉት ይገባል:: ስንቀ ነፍስ ያቀበሉት ታሞ ሊሞት የሚያጣጥ ርም ክርስቲያን ፈያታዊ ዘየማንን ይመስላል::

### ለ. ቆመውም በማስቀደስ የሚገኝ ክብር

ሥጋውን ደሙን ቢቀበሉም ባይቀበሉም በጸሎተ ቍርባን ጊዜ የአምላክን ምሕረት እየተለማመኑ ስርየትን እየፈለጉ ቆሞ ማስቀደስ ተገቢ ነው። (ፍ.መ.አ 13፥ 514) ምክንያቱም፦

በጸሎተ ቍርባኑ (በጸሎተ ቅዳሴው) ውስጥ ሆነን የለመነው ንም ልመና ፈጣሪ አምላክ ይሰማናል።

- ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን ለመቀበል ያበቃናልና፡፡
- ቆመን በማስቀደሳችን የቆምንበትን የቁመታችንን ዋጋ አያሳጣንም ቸር ነውና "ግነዩ ለእግዚአብሔር ወዘምሩ ለስሙ ልዑል እስመለዓለም ምሕረቱ" ለእግዚአብሔር ተገዙ እግዚ አብሔርንም አመስግኑ ምህረቱ ለዘለዓለም ነውና፡፡ (መዝ. 135 ቁ.1)

1. <u>ቆሞ የሚያስቀድስ ሰው ማንን ይመስላል?</u>

ጌታ ለስም አጠራሩ እስከዘለዓለሙ ክብር ምስጋና ይግባ ውና ቆሞ ደጅ ጠንቶ የሚያስቀድስ ሰው የእውነተኛ መምህራን ርእስ ምስጉን መምህር ክርስቶስ በከበረች ጸሎቱ ያመሰገነውንና የለመነውን የሰማውን ኀቤ ምእት (የመቶ አለቃውን) ይመስላል (ማቴ.8 ቁ 5-11)

የዚህም ሰው የተመሰገነች ጸሎቱም እንዲህ የምትል ነበረች "ጌታዬ ከቤቴ ጣራ በታች ትገባ ዘንድ አይገባህም" በአነጋገሩም ደስ የተሰኘው አምላክ "በቤተ እስራኤል መካከል እንኳ እንዲህ ያለ እምነት ያለው ሰው አላገኘሁም፤ ሂድ እንደቃልህ ይሁንልህ (ልጅህ ይፈወስልህ)" ብሎ በይቅርታ ቃል በደስታ አሰናብቶታልና።

<u>እንደዚሁም ኀጢአቱንና በደሉን በመታመን</u>

- ጌታዬ ቅዱስ ሥጋህን ክቡር ደምህን እኮ ብቀበል ፈቃዴ ነበር ነገር ግን በኀጢአት ስለረከስኩ "ከቤቴ ጣራ በታች ትገባ ዘንድ አይገባህም" በሚለው የተቀደሰ ልመና ቅዱስ ሥጋህን ክቡር ደምህን እበላና እጠጣ ዘንድ አይገባኝም!
- የቅዱስ ሥጋህና የክቡር ደምህ ማደሪያ ጻሕልና ጽዋ ለመሆን አልበቃሁምኮ!
- ነገር ግን በደሌን ሳትመራመር የቅዱስ ቍርባን ማደሪያ ጻሕሉና ጽዋውን እሆን ዘንድ በቸርነትህ ታበቃኝ ዘንድ ይቻልሀል ማለት ይገባል።

በእውነት ይህ ኀቤ ምዕት (የመቶ አለቃ) እኮ! ከቤቴ ጣራ ትገባ ዘንድ አይገባህም ብሎ የጌታን ታላቅነት የሱን ኢምንትነት በመ መስከር ፍጹም ትሕትናን ስላስተማረንና ጌታም የትሑታንን ጸሎት የሚወድ ስለሆነ ይህ ሰው የነፍስም የሥጋም አማላጅ በመሆኑን የሞተው ልጁ ተነሥቶለታል።

ስለዚህ ቆመን በማስቀደስ ኀጢአታችንን በማመን የእግዚ አብሔርን ምስጋና ከመላእክት ጋር ጸሎታችን ፍጹም በረከትን ያሰጠናል። ለሌላው ወገናችንም ይተርፋል ማለት ነው። ከአንጻረ መስቀሉ አጠገብ ቆመው በዕለተ ዓርብ የበረከተ መስቀሉ ተሳታፊ ዎች ከሆኑ ቅዱሳን በረከትን ያሳትፈን አሜን! (ሉቃ 23 ቁ.26-31

### ሐ. ቅዳሴ ጸበል

ከቊርባን በኋላ ቅዳሴ ጠበል ቅዱስ ቁርባን የተቀበሉት ሥጋወደሙ ሳያወርዱ ዛቲ መቅመስ አይገባቸውም፡ ስለዚህ አስተናጋጆች ሳለዕካነ ህግ ዲያቆናት በቅድሚያ ሥጋወደሙ የተቀበሉ ቁራቢዎች ካሉበት ከቦታቸው ሄደው ሐዳፌ (ነፍስን በመስቀ ትርክዛ እየቀዘፍክ ባሕረ እሳትን የምታሻግር የነፍሳት መምህር) የሚለው የመጨረሻ ጸሎተ ቊርባን የምስጋና ጸሎት ከተነበበ በኋላ ቅዳሴ ጠበልን ሊሰጧቸው ይገባል። (ፍት. መን. 13--65)

ለተቀሩት አስቀዳሾች ግን በእለተ ሰንበትም ሆነ በክብረ በዓላት እትዉ በሰላም (በሰላም ግቡ) ተብሎ ስንብት ከመሰጠቱ አስቀድሞ ወይም ከስንብቱ በኋላ ምቹ የሆነው ሰዓት ተመርጦ በማስተናበር ያሉ ዲያቆናትና ንፍቀ ዲያቆናት አስቀዳሾች ቆመው ባስቀደሱበት ቦታ እየሄዱ ለሁሉም በእየማእረጋቸው ያለሽሚያ ሊያድሏቸው ይገባል:: ይህ ከመምህራን የተገኘ ስርዋጽ ነው:: ሥርዋጽ-: ማለት የጠመመ ማቅኛ የጐደለ መሙያ አስተያየት ነው::

### መ. ቡራኬ

በጸሎተ ቅዳሴው ፍጻሜ ከቀዳሹ ካህን በእጆቹ መባረክ ይገባል::

ዲያቆኑ "አድንኑ አርእስቲክሙ ቅድመ እግዚአብሔር" በእግዚ አብሔር ፊት ራሳችሁን ዝቅ ዝቅ አድርጉ ካህኑ ይባርካችሁ ዘንድ ብሎ አዋጅ ያሰማናልና እኛም "አሜን እግዚአብሔር ይባርከነ ወይሠሃለነ" አዎን እግዚአብሔር ይባርከን ይቅርም ይበለን ብለን፤ ቡራኬውን ለመቀበል በረከተ እዴክ ቅድስት እንተ ምልእተ ምሕረት (በረከት) ኪያሃ ንሴፎ ኩልነ በረከት የተመላች እጅህን እርሷን ሁላችን ደጅ እየጠናን ነው እያልን በካህኑ እጅ እንዳሰሳለን እንባረክለን ::

ምክንያቱም ከካህኑ የጌታችንን ቅዱስ ሥጋውን እና ክቡር ደሙን በዳሰሰበት፤ በቆረሰበት፤ በፈተተበት፤ የከበረ እጆቹ ቡራኬ መቀበል ተገቢ ነውና:: ይኸውም በእጅ የመባረክን ሥርዓት ጌታ ደቀ መዛሙርቱን "እስከ ቢታንያ አወጣቸው እጆቹንም አንስቶ ባረካቸው" (ሉቃ.24 ቁ50) ብሎ ወንጌላዊው ከአስተማረን ሥርዓት የተወረሰ ነው::



የቡራኬው ተራ-:

- መጀመሪያ ካህናት
- ቀጥሎ ዲያቆናት አረጋውያን አባቶች እና ወጣቶች ወንዶች በየማእረጋቸው
- ከዚያም አአረጋውያት እናቶችና ወጣት ሴቶች በየማእረጋቸው ቆመው ከአስቀደሱበት ቦታ ካህኑ እየሄደ በእጆቹ ይባርካቸዋል:: በዚህ ጊዜ መጋፋት አግባብ አለመሆኑን ተገንዝበን ቡራኬውን መቀበል ይገባናል::